መጥቶ ጠባሳ እንኳን ቢያገኝ በር መትቶኝ ነው፤ አሳት ፈጅቶኝ ነው እያሉ እየሽፋፈኑ እየተቀጠቀጡ የሚኖሩ ሰላሉና እንዳንዶችም ከአስር ቤት ሲወጣ ይገለኛል ብለው ስለሚፈሩ የማይናገሩ ሰላሉ የዚህ የዚህ ዓይነት ሁኔታ ጥርጣሬ ውስጥ ስለሚከታቸው ነው ትንሽ ጫፍ ካገኙ እየደጋገሙ የሚደውሉት።

‹‹በሃሳብ ወደ አገሩ ነጎደና እኛ አገር በየመንደሩ የሚሰራውን ጉድ ዝርዝሩን አምጥቼ ለጀርመን ፖሊስ ማስረከብ ነበረብኝ››።

እያይ የኛን አገር የሴቶች በደልማ እናንሳው፤ እዚህ አገር እንኳንስ መደብደብ አይደለም ወደ ሆቴል እንኳን እየጣላት ብቻውን መሄድ ካዘወተረ ቀይ ካርዱን ነው የምታከናንበው፤ በርግጥ ፍቅር የሚሉት ጣጣ ብዙውን ሰው ማንነቱን ይቀይራል ይባላል፤ ነብር የነበረችው በግ ትሆናለች ነጋ ጠባ ስትቀጠቀጥ ጥፍሮቿ የት እንዳሉም ይጠፋባታል፤ ሮጣ ለማምለጥም አቅም ያላት አይመስላትም፤ እኔ በበኩሌ እንደ እነዚህ ዓይነት እህቶቼን አፍቃሪዎች ሳይሆን ልፍስፍሶች ነው የምላቸው።

ምን ልፍስፍሶች ብቻ ዘገምተኞች ናቸው እንጂ፤ እውነቱን ለመናገር የኛም አገር ፖሊሶች እናድርገው ቢሉ ብዙ ነገር ለማስተካከል የሚከብዳቸው ነገር የለም፤

አይ ነቢዩ የኛን አገር ፖሊሶች እንኳን ተዋቸው፤ ከስንት አንድ እንደነገብራይ ነው [redacted]

እዎ !



እንደነሱ ዓይነቱ ከስንት አንድ ካልሆነ በስተቀር ጉቦ የሚሉት መርዘኛ ነገር እንደፈንግጣ ከኢትዮጵያችን ብቻ ሳይሆን ከዓለም ላይ ካልጠፋ በስተቀር በትክክል ይሰራሉ ማለት ዘበት ነው።

እየሽ ጉቦ እኮ የትም አገር አለ፤ ለምሳሌ አሜሪካ ስሙን ቀይረውት ነው እንጂ ጉቦ በመቀባበል ከዓለም አንደኛ ነች ይባላል፤ በተለይ ይህ ክሪስመስ የተባለው በዓል እኛ አገር በአብዛኛው በመጽሐፉ ትዕዛዝ መሰረት በጾም ፣ በፀሎት እና መንፈሳዊ ስጦታ በመለዋወጥ [redacted] ሲሆን አሜሪካ ውስጥ ግን በተለየ መልኩ ትልቅ የጉቦ መቀባበያ ወቅት ነው፤ በአጠቃላይ በግልፅም በድብቅም ሆነ በእጅ አዙር ጉቦ በዓለም ላይ ሊጠፋ አይችል ። አንድ የማውቀውን ታሪክ ልንገርሽ አንድ ሰሞን አገራችን ውስጥ ግምገማ እናካሂድ ተባለና ደሞዝህ ይሄን ያህል ሆኖ ሳለ ቬራትን ገዝተህ በልተህ ጠጥተህ ስትወጣ ታይተሃል፤ ስደሬ ሄደህ ነበር ፣ ሱፍ በዚህ ያህል ገዝተሃል፤ ወደ ስራህ እንደ ሌላው ሰው አውቶቢስ ጠብቀህ አታውቅም ሁል ግዜ በታክሲ ነው የምትመላለሰው ይህን ሁሉ ወጪ ጉቦ ካልበላህ ከየት እምጥተህ ነው የምትሸፍነው? ተብሎ ሲገመገም፤ አሜሪካን አገር ያለ ጓደኛው ለአቅመ ደካማ ቤተሰቦቹ በእርሱ በኩል ብዙ ገንዘብ ይልክ ስለነበር፤ እኔማ እንደዚህ የምዝናናው በዌስተርን ዩኒየን በኩል የአጎቴ ልጅ በየጊዜው ከአሜሪካን ገንዘብ ስለሚልክልኝ ነው ብሎ የተላከበትን ደረሰኝ አሳይቶ ጎበውን መላጡን ቀጠለ እልሻለሁ፤ እና ጉቦን ማጥፋት ሳይሆን መቀነስ ከተፈለገ በተለይ ለፖሊሶች ትንሽ ደሞዝ ጨመር ማድረግ ያስፈልጋል በኛ አገር ሁኔታ ግን

ያላየናል ። እሺ ታዲያስ መለኮት እንዴት ነው ዛሬ በደንብ ሰላምታ ሳንለዋወጥ ወደ እቤቱ‐ታና ቀጣ ላይ የሮጥከው ?

ለነገሩ ስልክም እልሄን አስጨርሶኛል እዚህ ደግሞ የትርሲት ነገር ናዕላዬን አዞሮኛል ፤

ምን ተፈጠረ ደግሞ ትርሲት ደህና አይደለችም እንዴ?

እሱማ ደህና ነች የተለያየ ሰው ወሬ እየሰማች አስቸገረችኝ እንጂ ፤

የምን ወሬ እስቲ ግልጽልጽ አድርገህ ንገረኝ ፤

ምን መሰለህ ያው እንደነገርኩህ የመኖሪያ ፈቃዷን እስከምትጨርስ ድረስ እቤት ውስጥ መቀመጥ እንዳይሰለቻት ብዬ የአበሻ ሆቴል ውስጥ በነፃ እየሰራች ደንበኞች በሚሰጧት ጉርሻ ብቻ እንድትቆይ ብዬ እንዳስገባኋት ሳንተም ነግሬሃለሁ ፤

አዎን አውቃለሁ ፤

እና የሰማሁት ነገር ማመን እቅቶኝ በህልሜ ይሆናል እያልኩ እራሴን ለማታለል ብሞክርም እውነታው ከፊት ለፊቴ እየተደቀነ ልሸሸው አልቻልኩም ። ምነው መለኮት ለምን በማይመች በኮረኮንች መንገድ ትሄዳለህ ቀጥ ያለ አስፋልት እያለልህ ፤ የምትነግረኝን ለምን በቀጥታ አትነግረኝም ትርሲት ምን ሆነች ?

እሱማ ምን ትሆናለች እኔና አንተ ወጥተን ወርደን እዚህ አድርሰናት ግሪን ካርዷን የምታገኝበትን ሁኔታም አመቻችተን እያለን ፖለቲካ አይደለም መጠየቅ እምፈልገው አለች እልሃለሁ ።

ለምን እምቢ አለች ?



ምክንያቷ ብዙ ነው

1ኛው የኢትዮጵያ መንግስት ምንም ሳያደርገኝ ግለሰቦች በደሉኝ ብዬ እንዴት እከንነዋለሁ ሲሆን ሌላው 2ኛው የፖለቲካ ጥገኝነት ከጠየቅኩ ወደ አገሬ ለመመለስ እረዥም ጊዜ ይፈጅብኛል ነው የምትለው

ታዲያ ምን ይፈጠር አለች ?

እሷማ የምትለው የመኖሪያ ፈቃዴን በቀላሉ በጋብቻ ማግኘት እችላለሁ ነው

ለመሆኑ ይህን ሁኔታ ቀጭ ብላችሁ ረጋ በማለት ተወያይታችሁበታል ?

ኸረ በጭራሽ

ከየት አመጣኸው ታዲያ?

ትርሲት የምትሰራበት የአበሻ ሆቴል ውስጥ አብራት የምትሰራ እበራሽ የተባለች ጓደኛዋ ለጓደኛዋ አውርታለት ጓደኛዬ ነው የነገረኝ

ምንብሎነገረህ?

የሆቴሉ ባለቤት ትርሲት ስላሳዘነችኝ አፈርምላታለሁ ማለታቸውን

ከልቡ ለመርዳት የሚያደርገው ከሆነ ታዲያ ቢፈርምላት ምን አለበት ?

የእውነታቸውን እንዳልሆነ ብዙ ምልክቶች አሉ ።

ያው አብዛኛው ሰው እንቱ ሲላቸው ደስ የማላቸው ሰውዬ ትርሲትን አንተ በይኝ ብለው መቅጣቻቸውን እራሷም ነግራኛለች ፤ ከዚያም በተጨማሪ በረቀቀና በተቀነባበረ መንገድ ልታመልጥ እንዳትችል ጠንካራ

ደግሞ... መልሷ አረ አባካችሁ ደግሞ ብላችሁ ብላችሁ ስለካፒታሊዝም ተከራካሪ ሆናችሁ?

እንዴ አምሳልዮ ታዲያ ሶሻሊዝምን እናድንቅ? እንኳን ልከራከርለት ከዓለም ላይ በአጠቃላይ ሊጠፋ ትንሽ አገሮች ጭር እንዳለች ዶሮ ታቅፈውት ቢነጫነጩም በጥቂት ግዜ ውስጥ ፈንግል ይፈነግላቸዋል እሱንማ ስሙንም ባትጠሪው ደስ ይለናል። ሶሻሊዝም ብሎ ጣጣ አገራችንስ ቢሆን አዘቅት ውስጥ የጨመራት እንዲህ በቀላሉ የሚረሳ ሆነ።

አያችሁ ስለሶሻሊዝም ረቀቅ ያለ ግንዛቤ ያላችሁ አይመስለኝም። ሶሻሊዝም በጣም የተጠላና መኖር የሌለበት ቢሆን ኖሮ ካፒታሊስት አገሮች ስለመጥፎነቱ ምንም ዓይነት ቅስቀሳና ፕሮፖጋንዳ ገንዘባቸውንና ጊዜያቸውን አያጠፉም ነበር ምክንያቱን ጥሩም ሆነ መጥፎ ነገር ማስታወቂያ እያስፈልገውም። በቅስቀሳው ብቻ ማሸነፍ ስላቃተቸው አይመስላችሁም፤ አሜሪካኖች ቤትናም ጦራቸውን መዘው ሄደው ስንትና ስንት አሜሪካኖች ህይወታቸውን ያጡት አንድ ነገር ማስታወስም ይኖርባችኋል። "ካፒታሊዝም የሶሻሊዝም ጥሩ ጥሩ መርኮዎች እስከአሁን እንደሚጠቀሙባቸውም መገንዘቡ የሚሳናችሁ አይመስለኝም፤

እንዴው ወሬን ወሬ ሲያነሳው ዘለን ፖለቲካ ውስጥ ገባን እንጂ እኔ ወደ ኢትዮጵያ ከመሄድ ጋር ያን ያህል የጎላ ግንኙነት ያለው አይመስለኝም ፡፡

እንዴ ምን ማለትሽ ነው ፖለቲካና ኑሮማ ተለያይተው እያውቁም የሰው ልጅ ልብስ ሳይለብስ እራቁቱን እንዴት ሊኖር ይችላል ሲሉ ሌላው ቀበል ብሎ የሰው ልጅ ዕድሜው



ቶሎ ቢቀጭም ካለልብስ ኖሮ ያውቃል "ፖለቲካ እንደ አጥንትና ስጋ" ብትለብሰው ይሻላል ልክ ነህ እንዱ ካለ ሌላው ፈፅሞ ሊኖሩ አይችሉም ሲባባሉ ነው ጊዜያቸውን የሚያጠፉት ባገኙት አጋጣሚ በተገኛኙ ወይም በተደዋወሉ ቁጥር ፡፡

ስለ ትርሲት ሁኔታ አቶ ነቢዩ ሲያጫውታት እጅግ በጣም ብታዝንም አሜሪካን ለመምጣት የከፈለችውን መስዋዕትነት ግን እንደለማችው ከሆነ ብዙም አልጣማትም ፤ ሙሉ በሙሉ መምጣቷን ለመቃወም ደግሞ ህሊናዋ ሙግት ገጥሟት አሸንፏታል ፤ ገና ትርሲትን ስታያት ደግሞ የባሰ ተሸንፋለች ፤ ትርሲት ገና ሲያደት አውሬው እንደሰው ሰው እንደ አምላክ እንዲያስብ ታደርጋለች የተለይ መስህብ አላት እለ እይደል ሁለመናዋ ያሳዝናል ፡፡

ወ/ሮ አምሳለ ብዙም ጊዜ ሳታጠፋ ነበር እሺ አሜሪካንን እንዴት አየሽው ያለቻት

ውይ አሜሪካ ሁል ጊዜም እንደዚሁ ከሆነ በተለይ ለኔ ብዙም ለውጥ የለውም

ለትይ ?

ማለቴ በተለይ ሌላውን ገና ስርቼበት አላውቅም ፤ የሀበሻ ሆቴል መስራት ማለት ትንሽ ያለኝ ጥቅም ስሜቴን በቋንቋዬ መግለጽ ካልሆነ በስተቀር ለኑሮ መታከቱ፡ መልፋቱ፡ ወገብን መንቀጥቀጡ ፤ እንቅልፍ በደንብ አለመተኛቱና ስቆቃው ከአረብ አገሩ ባርነት ጋር ሲነጻጸር ያን ያህል ልዩነቱ አይታየኝም ፤

አይዞሽ የኔ እህት ሁሉም ነገር በእግዜአብሔር ቸርነት መልኩ መልክ ይይዛል ፤

ትርሲት በድንገት ኑሮ "የራሱ ጉዳይ" ብላ ጭንቅላቷን ወደ መሬት አቅርቅራ የግራ እጇን ክንድ እጭና ላይ በመዳፏ ጭንቅላቷን ደገፍ አድርጋ ያው የተለመደ የደም እንባዋን ስታወርደው፤

ተይ እንጂ የኔ እመቤት አይገባም! እየነገርኩሽ ከላስቬጋስ ድረስ አምስት ሰዓት ሙሉ ለምን ነድቼ የመጣሁ ይመስልሻል? እባክሽ በቃሽ ለቅሶ ምን ያደርጋል? ተይው እልኩሽ እኮ!

ምናባቱ! ይልቅስ እንጂ ማለቂያ የሌለው እንባ አሁንስ ከመቼውም በላይ መረረኝ ፤ የኔ ህይወት ምንድ ነው ? አባቴም ያመነው ለው ሁሉ ከድቶት ተቃጥሎ ሞተ ልክ በዘር እንደሚተላለፍ በሽታ ይኸው እኔም ህይወቴን እስጥለታለሁ ያልኩት እንደ ንፁህ ወንድሜ የማየው ሰው ሁሉ እየከዳኝ እየተለወጠብኝ እያየሁ ነው እኮ የኔ መኖር የቱ ጋር ነው ትርጉሙ?

እንግዲህ ከሰማሽን ታገሺ ብዬሻለሁ ፤ እንድ መርሳት ሁል ጊዜ በአዕምሮሽ ማስቀመጥ ያለብሽ ነገር ቢኖር ስለቆንጆዎች ነው ፤

እየሽ ቆንጆዎች ላያቸውና ለሚገምታቸው ሰው ሁሉ ለነሱ ብዙ ነገር ቀላል ስለሚመስላቸው በየሄዱበት በየስራቸው ቦታ ሁሉ እነሱ በፈለጉት መንገድ እያከናወኑ ተዝናንተው እንደሚኖሩ ነው የብዙው ሰው አመለካከት ፤

በተረጋጋ መንገድ ለገመገመው ግን ቀን በቀን የጭንቀት ፤ የውጥረት ህይወት የሚኖሩት ቆንጆዎች ናቸው ። ማንኛውም ሰው ባገኘው አጋጣሚ ከቆንጆዎች ጋር መሆን



ይፈልጋል ያያቸው ለለነሱ ውበት የሰማው ሁሉ እነሱ በግድም በውድም በጥቅም ቆንጆዎችን ማግኘት ይፈልጋል ፤ ባጭሩ የቆንጆዎች ጣጣቸው ብዙ ነው እንደዚህ የመሳሰሉትን ክስተቶች በብልኀት ማሳለፉ ደግሞ የናንተው የቆንጆዎች ድርሻ ይሆናል ብላ ፈገግ ብላ በመቀጠል በቆንጆዎች ላይ የተሰራውን ወንጀል ታጥቆ መድፈሩን ብቻ ሳይሆን በተለይ በእህቶቻንች ፊት ላይ አሲድ የተረጨበትንም ሁኔታ ማስታወሱ ጥሩ ማስጠንቀቂያና ትምህርት ሊሆን ይገባዋል።

ወ/ሮ እምሳለ በግራ እጇ መሪውን ይዛ ቀኝ እጇን እያወዛቀዘች ፡ እውነቱን ለመናገር ወደድሽም ጠላሽም ዩ እር ኢን ኤ ላንድ እፍ አፖርቹኒቲ ወደ መስፋፋቱ ምድር መጥተሻል ማለቱ ነው። አሜሪካ ደግሞ እውነቱን ለመናገር በጣም ጥሩ አገር ነው፤ ከተሰራ ገንዘብ ይገኛል ፤ ተምረሽ በትምህርትሽ ከነበዝሽ ከፍ ያለ ደረጃ መድረስ ትችያለሽ በማንኛውም መስሪያ ቤት እስፈላጊውን መስፈርት እስከሟላሽ ተቀጥሮ መስራት ይቻላል እንደኛ አገር የጉራጌዎች የአማራዎች ፡ የትግሬዎች ባንክ ነው የምባል ነገር የለም ፤

አሜርካኖች ህጋቸውም በጣም ጥሩ ነው። ከዛሬ ሁለት መቶ ዓመት በፊት ያወጡትን ህግ እስከ እሁን እየተጠቀሙበት ነው። እብዛኛው ሰው ለህግ ተገዢ ነው ፤ ባጠቃላይ አሜሪካን የፈለግሽው መሆን የምትችይበት አገር ነው ። ለዚህም ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን በግ ጠባቂ ሆኖ ያደገው ኬንያዊ አሜሪካን መጥቶ ዶ/ር እስከሚሆን ተምሮ ከዚያም ከአሜሪካዊ ጋር በመጋባት ልጅ ወለደ የወለደውም ልጅ

ሊያስቆጥረው አይገባም እኛም እንደባላጋራችን ልናየው አይገባም ::

አረ በስማም ስትል ትርሲት በድንገት በጣም ጥሩ ይህ ዓይነት አስተሳሰብ ነው የሚያስፈልገው ፤

አንቺን ከሱስ እንጀሰስ ወደ ላስ ቬጋስ እንድትሄጂ ከነቢዩ ጋር ከተመካከርንባቸው ብዙ ምክንያቶች አንዱ ከመለኮት ጋር ለማለያየትም ነው ምክንያቱም አብራችሁ ከኖራችሁ ፍቅር መላመድም ነውና ሌላ መዘዝ ውስጥ ይገባል ይህን ሁኔታ አንችም እንደሰማሁት ከሆነ በቃል ኪዳን የታሰርሽ ስለሆነ ፈፅሞ አትፈልጊውም ::

እህ ! ጭራሽ ለምንስ ታስበ ? !

ለማንኛውም ለሞኑን ለኢሚግሬሽን ቃለ መጠየቅ ስንመጣ አብረን እናገኘውና ለውጡን እናያለን እርግጠኛ ነኝ ከአጠገቡ ዞር ስላልሽ ፍቅር አቃጠለኝ ሳላያት ውዬ ካደርኩ ምግብም የምበላ አይመስለኝም ምንትሴ የሚለው ነገር እንደሚለቀው ነው ::

ኸረ እሱ ደረጃ እንኳን አስልደረሰም ነበር ፤ አንድ ሁለት ቀን ከወንድም የማይጠበቅ ነገር ከማድረጉ በስተቀር

እሱን እንኳን ተይው ፤ የሚናገረውንና የሚያስበውን ብቻ ሳይሆን በየቀኑ የሚበላቸውን የምግብ ዓይነቶች ሳይቀሩ ይደርሱን ነበር ፤ የሚገርምሽ መለኮት ደግነቱ ለችግር ደራሺነቱ ከወደደሽ ነፍሱን ሰመስጠት አለመነሳሳቱ ሳያንሰው ቅልጥፍናው ለቆንጆዎች ያለውን አመለካከት ነቢዩም ብዙ ስለማይወደው ከሱ ጋር ከሆንሽ ጀምሮ በስውር የሚከታተሉሽ



ሰዎች መድበን ስለሁኔታው አንች ከነገርሽን በላይ ብዙ በጣም ብዙ መረጃዎች አሉን ::

እሱማ በመጠኑም ቢሆን በተለይ ትላንትና ዛሬ ያየሁት ቅልጥፍና ለኔ ብዙ እንደደከማችሁልኝ ይገባኛል ::

የኔ ቆንጆ የኛ ድካም ለአንች ብቻ ሳይሆን ለራሳችንም ነው ፡ "እርዳታ የሚፈልግን ሰው እርድተሽ የሚገኝ ደስታ ዘላለማዊ ነው" በእርግጥ የደስታ ዓይነቶች ብዙ ዓይነቶች ሲሆኑ ሰዎችን የሚያስደስታቸው የደስታ ዓይነቶችም እንዲሁ ብዙ ሆነው ዓይነታቸውም እንደሰው ይለያያል :: እያንዳንዱ ሴቶች እህቶቻችንን አንቆ ደፍሮ ለአስምስትና ለአስር ደቂቃ የርኩስ የረከሰ ስሜቱን አርክቶ ይህንንም ከደስታ የሚቆጥር ሲጠጣ ሲጨፍር የሚያድረው ከአገር አገር እየዞር የሚዝናናው ጠያቂ የሌላቸውን ህመምተኞች በየሆስፒታሉና በየቤታቸው እየዞረ የሚጠይቀውን የሚላስ የሚቀመስ ለሌላቸው ደኻዎች አቅሙ እንደፈቀደ የሚያካፍለው እንግዳን የማስትናገዱ ሁሉ እርሱ ለማሰደት ቢሆንም የቶቹ ይቅሩ የትኛዎቹ ይከናወኑ ደግሞ የለው ልጆች ምርጫ ሲሆን እንዳልኩሽ ጥሩ ምርጫ በመስራት የሚደሰተው የተሰራለት ብቻ ሳይሆን ሰሪውም ነው ለማለት ነው ::

ትርሲት ጣቶቿን እያፍተለተለች --- ከንፍሮቿ እየተንቀጠቀጡ "ሁሉ ሰው እንደናንተ ቢሆን ኖሮ የኛ አገር ብቻ ሳትሆን የዓለም ህዝቦች ሁሉ ሳይራቡ ሳይጠሙ ችግር ሳይገባቸው ይኖሩ ነበር ::

እሱማ አይሆንም እንጂ ቢሆንም ኖሮ በዓለም ላይ በተለያየ አገር የሚኖሩ መቶ እና ሁለት መቶ የሚሆኑ የተለያዩ

ዘዴ በመጠቀም ያካበቱት ኀብታቸውን የተቸገረ ሁሉ ይጠቀምበት ብለው ቢለቁት በሚሊዮን የሚቆጠሩ የዓለም ህዝቦች በረሃብና በውሃ ጥም ከሚሞቱ ህይወታቸውን ያትርፉላቸው ነበር ::

እሱን እሱን ካነሳንማ ለለ እኛ አገር ሀብታሞች እንኳን ብዙ ማለት ይቻል ነበር ፤

ሀብታሞች በኛ አገር ብቻ ሳይሆን እንዳልሺው በተለያዩ አገር ያሉት ሁሉ አስገራሚዎች የሚገርሙና የሚደነቁ ናቸው ሀብታቸው እንኳንስ በስመ የአገር ልጅነት ሊያካፍሉ አይዞህ ሊሉ ቀርቶ በደም በስጋ የሚዛመዱት ወንድማችው ማደሪያ አጥቶ ሲንከራተት የነሱ ውሾቻቸው መጠለያ አግኝተው ወገናቸው የጎማ ጫማን መግዢያ አጥቶ በባዶ እግሩ ሲኳትን እነሱ የመኪና ዓይነት ሲያማርጡ በረሃብ አለንጋ ሲገረፍ፤ ውሻቸው ቁርሱን ምሳውን ምን በላ የሚሉ ቀጥራቸው መች በቀላል ይገመትና የሚገርምሽ እንደነዚህ ያሉ ባለ ሀብቶችን ይቅርታ አድጊልኝና አስተሳሰባቸውን ከቀረው ህዝብ ጋር ለማመሳሰል በጣም ይከብደኛል ::

ለወ/ሮ አምሳለ መልስ ለመስጠት ፊሩ ተባ እያለች የሀብታሞች አስተሳሰብ ከመላው ማህበረሰብ ጋር ልዩነት እንዳለውማ ጥርጥር የለውም ምክንያቱም የተለይ ሀብት ያከማቹት የተለየ ባህርይና የአሰራር ስልት ስላላቸው ነው በመሰረቱ ማንኛውም ሰው ሀብታም መሆን ይመኛል ሀብቱን የሚያገኙት ደግሞ እነዚህ ጥቂት ቁልፉን ያገኙት ብቻ ናቸው :: እዚህ አገር ስትቆይ በሀብት ዙሪያ ብዙ ነገር ትገነዘቢያለሽ ፤ በእርግጥ እዚህም አገር አለመተዛዙኑ እልፍ እልፍ ይታያል::



አሜሪካን ውስጥ ለለመተዛዘን ባነሳሁ ቁጥር ሁል ግዜ የሚደንቁኝና የሚያሳዝኑኝ የአሚሽ ህዝቦች የተባሉት ጎሳዎች አሜሪካን ውስጥ እንዴት እንደሚኖሩ ነው ::

አሚሾች በስልጣኔ የመጠቀችው አሜሪካን ውስጥ ቢኖሩም የዕለት ተዕለት ኑሯቸው ግን እኛ አገር የኤሌክትሪክ መብራት ፤ ስልክ ፤ መኪና ፤ ዘመናዊ ህክምና ባጠቃላይ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ለመሆን ያልታደለው ክዚያ ምስኪን ወገናችን የባሰ የጨለማ ህይወት ነው የሚኖሩት ፤

በርግጥ " የአሚሽ ህዝቦች " ቴክኖሎጂን "አይንህን ላፈ " ብለው የሚኖሩት የእገሩ ህግ ወይም ሀብታሞች ተዕለና አድርጎባቸው ሳይሆን የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ሳለመሆን ካላቸው ጽኑእምነትእንጻርነው::

ትርሲት የምትነግራትን ታሪክ ማመንና መቀበል አቅቷት " የምርሽን ነው ወ/ሮ አምሳለ የምትነግሪኝ ?"

በጣም እንጂ እኔም መጀመሪያ ለለ አሚሾች ለለማ ማመን አቅቶኝ፤ ይኖሩባቸዋል የተባሉት ክ/ሀገሮች ሄጄ ካየኋቸው በኋላ ነው ማየት ማመን ነው እንዲሉ የተገረምኩትና የተደነቅሁት ለማንኛውም በላልተን እንውጣና ወደ ላስ ቬጋስ ለመድረስም ወደ አምስት ሰዓት ገደማ ስለሚፈጅብን በሰፊው እንጫወታለን ::

ልክ ነሽ ካላዩት ማመን ያስቸግራል ወደ አሜሪካን መጥቶ የቴክኖሎጂው ተጠቃሚ ለመሆንና ኑሮውን ለማሻሻል ስንቱ ደሃ ነው አገሩን ጥሎ እምባ ገነኖችን ሸሽቶ ድንበር ሲያቋርጥ በየበረኻው በውሃ ጥም ተቃጥሎ የሚወድቀው በአውሬ የሚበላው ፤ የተሳፈረበትን ጀልባ ማዕበል

